Arlington Public Schools

# በቅድመ መዋለህጻናትና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት ተግባቦት

**የወላጅ መገልገያ ማእከል** (**PRC**) የልዩ ትምህርት ሂደትን ክትትል ለማድረግና *ጥያቄዎችን/ስጋቶችን ለመፍታት ምክር ለመፈለግ ለሁሉም ቤተሰቦች ኢጋዥ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ከማን ጋር እንደሚነጋገሩ እርግጠኛ ኢይደሉም? የእውቂያ መረጃ ይፈልጋሉ? ጥያቄ ወይም ስጋት አለዎት?* PRC በ mailto:prc@apsva.us ወይም 703.228.7239 ያግኙ፡፡

ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠትና ችግሮችን ለመፍታት በመተባበር ከልጅዎ መምህር፣ ከጉዳይ አገልግሎት አቅራቢ ወይም ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪ (*ጉዳዩ ተዛማጅ አገልግሎትን ኢካቶ የሚይዝ ከሆነ*) መጀመር ሲቻል ሁልጊዜ የተሻለ ይሆናል፡፡

**የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ** (*ለትምህርት ቤትዎ የተመደበው የማእከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኛ*) ችግሮችን ለመቅረፍ ቡድኖችን መደገፍ ይችላል፡፡

***ተጨማሪ እገዛ ይፈልጋሉ?*** በቀኝ በኩል ያለው ቻርት የሚመከር የግንኙነት ቅደም ተከተል ያቀርባል፡፡ በቅደም ተከተል ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ከ IEP ቡድን አባላት ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች (ማለትም የመመሪያ አማካሪዎች፣ የትምህርት ቤት የስነልቦና ሐኪሞች፣ ልዩ ባለሙያዎች፣ ወዘተ) ጋር እውቀትንና ድጋፍን ሊሰጡ ከሚችሉ ባለሙያዎች ጋር እንዲገናኙ ሊጠቁሙ ይችላሉ፡፡

የ APS ክፍል ድርጅታዊ ቻርት

1. መምህር/ጉዳዩን የያዘው/ተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢ
2. የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ (SSC)*
3. ረዳት ርእሰ መምህር
4. ርእሰ መምህር
5. የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር*
6. ዋና የትምህርት መኮንን*
7. ተቆጣጣሪ*
8. የትምህርት ቤት ቦርድ*

* የዲስትሪክት ደረጃ ሰራተኞች

የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (ASEAC) የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ትምህርት በተመለከተ ለ APS የሚያሳውቅ ሲሆን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮችን እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ፍላጎቶች እንዲሟሉ ለማድረግ ስልቶችን በማዘጋጀት ተሳትፎ ያደርጋል፡፡